11 ኛ ዓመት ቁጥር 12

ባህርዳር መጋቢት 30 ቀን 1998 ዓ.ም
Bahir Dar 8 2006

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ሕግ

ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State	✉ 312 ያንዱ ዋጋ ብር 2.30 Unit price	

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 127/1998 ዓ.ም

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት 2 ኛ ማሻሻያ ማፅደቂያ አዋጅ

አዋጅ ቁጥር 127/1998 ዓ.ም

የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግ ስት 2 ኛ ማሻሻያ ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ በተ ሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ መንግስት አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 3 እና አንቀጽ 100 ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር እንዲተደነገገው የወረዳና የቀበሌ ም/ቤቶች የአገልግሎት ዘመን በ 5 ዓመት የተወሰነ በመሆኑ፣

በሕገ-መንግስቱ መሠረት ይኸው የአገልግት ዘመን ከማብቃቱም ከአንድ ወር በፊት የተተኪ.
ምክር ቤቶች ምርጫ ተካሂዶ በመጠናቀቅ ያለበት ሲሆን በተቃራኒው ሂደቱን የሚያጓትት ወይም ውጤቱን የሚያዛባ ነባራዊ ሁኔታ ቢያጋጥም ምርጫውን ለሌላ ጊዜ ለማስተላለፍና የተሰናባች ምክር ቤቶችን የሥራ ዘመን ለማራዘም የሚያስችል እድል ያልተሠጠ ሆኖ

ከዚህ በመነሳት የክልሉ ምክር ቤት በመርህ ደረጃ የተወሰነውን ይህንኑ የ 5 ዓመት የአገልግሎት ዘመን ጠብቆ እንዳስፈላጊነቱ ምርጫውን ሌላ ጊዜ ማስተላለፍና የነባር ምክር ቤቶችን የሥራ ዘመን ማራዘም ያቻለው ዘንድ ለጉዳዩ አግባብነት ያላቸውን የሕገ-መንግስቱን ድንጋጌዎች መርምሮ ማሻሻል በማስፈለጉ፤

በተሻሻለው የብሔራዊ ክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ እና አንቀጽ 118 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዊች መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ"የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ

ክልል ሕገ-መንግስት 2ኛ ማሻሻያ ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር 127/1998 ዓ.ም” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2.ማሻሻያ

በአዋጅ ቁጥር 59/1994 ዓ.ም አማካኝነት የፀደቀውን የተሻሻለው የአማራ ብሔራዊ ክልል ሕገ-መንግስት ለ 2ኛ ጊዜ በዚህ አዋጅ እንደሚከተለው ተሻሽሏ፡፡

ሀ. ከህገ መንግስቱ አንቀጽ 89 ንዑስ አንቀጽ 3 ቀጥሎ ሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 የገባ ሲሆን በዚሁ ተጨማሪ ድንጋጌ መካተት ሣቢያ ቀድሞ ንዑስ አንቀጽ 4 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5 ሆኖ ተስተካክሏል፡፡

4 በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተደነገገው ቢኖርም የወረዳው ምክር ቤት የገልግሎት ዘመን በበቂና አሠማኝ ምክንያት መኖሩ እየተረጋገጠ እንዳስፈላጊነቱ በሚተላለፍ የክልሉ ምክር ቤት ውሣኔ ላልተወሰነ ጊዜ በልዩ ሁኔታ ሊራዘም ይችላል፡፡

ለ. ከሕገ- ምንግስቱ አንቀጽ 100 ንዑስ 3 ቀጥሎ ከዚህ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 4 የገባ ሲሆን በዚሁ ተጨማሪ ድንጋጌ መካተት ሣቢያ ቀደሞ ንዑስ አንቀጽ 4 የነበረው ንዑስ አንቀጽ 5 ሆኖ ተስተካክሏል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ሥር የተደነገገው ቢኖርም የቀበሌ ምክር ቤት

የአገልግሎት ዘመን በቂና አሣማኝ ምክንያት መኖር እየተረጋገጠ እንዳስፈላጊነቱ በሚተላለፍ የክልሉ ምክር ቤት ውሣኔ ላልተወሰነ ጊዜ በልዩ ሁኔታ ሊራዘም ይችላል።

3. ማሻሻያ ስለ ሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ማሻሻያ በክልሉ ሕገ- ምንግስት አንቀጽ 118 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌዎች መሠረት የበታች ም/ቤቶችን ይሁንታ አግኝቶ በክልሉ ምክር ቤት ከፀደቀና በዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
መጋቤት **30** ቀን **1998** ዓ.ም

አያሌው ጐበዜ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት